ይህቺ ጂኒ የሚሰርቃት የእውነት ንግግር ናት። በወዳጁ ጆሮ ውስጥም ዶሮ ጩኸቷን እንደምትደጋግመው ይደጋግምለታል። በዚህች እውነት ውስጥም ከመቶ ውሸት በላይ ይቀላቅሉበታል።'

ከእናታችን ዓኢሻህ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- እንደተላለፈው እንዲህ አለች: "ሰዎች የአላህን መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ስለጠንቋዮች ጠየቁ። የአላህ መልክተኛም ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ለነርሱ 'ምንም አይደሉም።' በማለት መለሱ። እነሱም
'የአላህ መልክተኛ ሆይ! አንዳንድ ጊዜ አንድ ነገር ተናግረው እውነት ይሆናል።' አሉ። የአላህ መልክተኛም ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም
እንዲህ አሉ ' ይህቺ ጂኒ የሚሰርቃት የእውነት ንግግር ናት። በወዳጁ ጆሮ ውስጥም ዶሮ ጩኸቷን እንደምትደጋግመው ይደጋግምለታል።
በዚህች እውነት ውስጥም ከመቶ ውሸት በላይ ይቀላቅሉበታል።'" [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ለወደፊት ስለሚከሰቱ የሩቅ ሚስጥራት ስለሚናገሩ ሰዎች ተጠየቁ። እሳቸውም: ቦታ አትስጡት ፤ ንግግራቸውን አትያዙ፤ ጉዳያቸው አያሳስባችሁ አሉዋቸው። ሶሐቦችም "በእንዲህ ወርና በእንዲህ ቀን" ብለው የሩቅ ሚስጥር ጉዳይ እንደሚከሰት እንደሚናገሩና እንደተናገሩት ገጥሞ መከሰቱን አይነት ንግግራቸው አንዳንድ ጊዜ ተጨባጩን የሚገጥም መሆኑን ተናገሩ። ነቢዩም ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለምም እንዲህ ብለው መለሱላቸው "ጂኖች ከሰማይ የሚሰሙትን ወሬ በመስረቅ ወደ ጠንቋይ ወዳጆቻቸው አውርደው የሰሙትን ይነግሯቸዋል። ከዚያም ጠንቋዩ ከሰማይ በሰማው ላይ መቶ ውሸት ይጨምርበታል።"

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/8918